# 2024 ሲያትል የመጓጓዣ ቀረጥ

City of Seattle

ነሐሴ 2024

በሲያትል መራጮች የጸደቀ ከሆነ፣ የ2024 ሲያትል የመጓጓዣ ቀረጥ 8 ዓመታት በሚያልፍ ጊዜ $1.55 ቢሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ በሲያትል ውስጥ የመጓጓዣ ማሻሻያዎችን ያስገኛል። ይህ የእውነታ ወረቀት የመዋዕለ ንዋይ አካባቢዎችን በፕሮግራም እና የመጓጓዣ ቀረጥ ድጋፍ ገንዘቡ የሚውልባቸው ምሳሌዎችን አጉልቶ እንደሚያሳይ ይገልፃል።

- ባለፉት 18 ዓመታት፣ የሲያትል መራጮች ለመንገዶቻችን፣ ለእግረኛ መንገዶች፣ ለድልድዮች እና ለትራፊክ ምልክቶች ጥገና እና ማሻሻያ የሚደረጉትን የገንዘብ ድጋፍ የመጓጓዣ ቀረጦችን ደግፈዋል።
- አሁን ያለው ቀረጥ በ2024 መጨረሻ ላይ ያበቃል እና አንኳር ለሆኑ አገልግሎቶች እና ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች 30% የሚሆነውን የሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ (SDOT) በጀት ያቀርባል።
- የመጓጓዣ ቀረጥ እንደ የመንገድ ንጣፍ መዘርጋት፣ ድልድይ መጠገን፣ ዛፎችን መትከል፣ የእግረኛ መንገዶችን እና የእግር መሻገሪያዎችን መገንባት፣ ወደ ቀላል ባቡር ጣቢያዎች እና የሕዝብ መጓጓዣ የሚደረገውን ግንኙነት መፍጠር እና ተጨማሪ የእግር መሄጃ፣ የማንከባለል እና የቢስክሌት መስመሮችን በመፍጠር ሰዎች ወደሚኖሩበት፣ የሚሰሩበት እና የሚጫወቱበት ማሻሻያ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ነው።
- የማህበረሰብ የቀረጥ ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን ለማረጋገጥ የመጓጓዣ ቀረጥ ዶላር ወጪዎችን በበላይነት ይቆጣጠራል። እንዲሁም SDOT የመጓጓዣ ቀረጥ ዶላሮች እንዴት እንደሚወጣ ለሕዝብ ለማሳየት ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶችን እና የሂደት ሪፖርቶችን ያትማል።

## የመጓጓዣ ቀረጡ ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ

ቀረጦቹ ቀረጦቹ የሚከፈሉት በሲያትል ንብረት ባለቤቶች ነው። ጊዜው እያለፈ ባለው የመጓጓዣ ቀረጥ መሠረት፣ በመካከለኛ ግብር የተገመገመ ዋጋ ቤት ያለው ባለቤት በግምት በወር $23 ዶላር ገደማ ይከፍላል። ለ 2024 የመጓጓዣ ቀረጥ የተገመቱ ወጪዎች:

| | | |
|---|---|---|
| **$54** | **$44** | **$27** |
| በወር<br>**$1,000,000 ዶላር ለሆነ ቤት** | በወር<br>**$804,000 ዶላር አማካኝ ዋጋ ለሆነ ቤት** | በወር<br>**$500,000 ዶላር ለሆነ ቤት** |

AMHARIC

# የመጓጓዣ ቀረጥ እንዴት ወጪ እንደሚደረግ ዕቅድ

የመጓጓዣ ቀረጥ በ11 የፕሮግራም ዘርፎች ተደራጅቷል፣ እና እያንዳንዳቸው ፕሮጀክቶችን ያቀርባሉ። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል አንዳንዶቹ ተወስነዋል፣ እና ብዙዎቹ ወደፊት ተለይተው ይታወቃሉ።

በመጓጓዣ ቀረጥ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ለመምረጥ፣ SDOT የተቋቋሙ የከተማ ፖሊሲዎችን ጨምሮ የተለያዩ ነጥቦችን/ ምክንያቶችን ይጠቀማል። SDOT በሲያትል የዘር እና የማህበራዊ ፍትሃዊ እኩልነት ጠቋሚ መረጃ እና የመጓጓዣ ፍትሃዊ እኩልነት ማዕቀፍ የተነገረውን የቀረጥ መዋዕለ ንዋይ በፍትሃዊ እኩልነት ለማከፋፈል ያልማል።

**ከ8 ዓመት በላይ**
**$1.55 ቢሊዮን ዶላር**



# የመጓጓዣ ቀረጥ ፕሮግራሞች

የመጓጓዣ ቀረጥ 11 የፕሮግራም ዘርፎች በተለይ የተወሰኑ መዋዕለ ንዋዮች፣ እንዲሁም የወደፊት ፍላጎቶችን ለመፍታት ተለዋዋጭነትን ያካትታሉ። SDOT የመጓጓዣ ቀረጥ አካል የሆኑት መገንባት የሚቻላቸውን ፕሮጀክቶች እጅግ ከፍ ለማድረግ የማበረታቻ እድሎችን ሚዛናዊ እንዲሆኑ ይሻል።

**ራዕይ ዜሮ፣ ትምህርት ቤት እና የሰፈር ደህንነት ($160.5ሚ ዶላር):-** የትራፊክ ግጭቶችን፣ ከባድ ጉዳቶችን እና የሞት አደጋዎችን ለመቀነስ የታለሙ እና በማህበረሰብ የተጠየቁ መንገዶች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ መስቀለኛ መገናኛዎች እና ማቋረጫዎችን ማሻሻያዎች ማድረግ።

**የመንገድ ጥገና እና ዘመናዊነት ($403ሚ ዶላር):-** አብዛኛውን አውቶብሶችን፣ የጭነት መኪናዎችን እና መኪኖችን የሚሸከሙ አገናኝ መንገዶችን እንደገና ንጣፍ ማድረግ፣ እና በእግር ለሚሄዱ፣ የሚያንከባልሉ፣ ቢስክሌት ለሚጋልቡ እና የሕዝብ መጓጓዣ ለሚወስዱ ሰዎች መሠረተ ልማትን ማሻሻል።

**ድልድዮች እና መዋቅሮች ($221ሚ ዶላር):-** ድልድዮችን እና መዋቅሮችን በሚሰራ አስተማማኝ ሁኔታ ማቆየት እና ለወደፊት ድልድይ ፕሮጀክቶች ማዘጋጀት።

**የሕዝብ መጓጓዣ ኮሪደሮች እና ግንኙነቶች ($151ሚ ዶላር):-** የሊንክ (Link) ቀላል ባቡር ጣቢያዎችን እና የአውቶቡስ ማቆሚያ ጨምሮ ሰዎችን በደህና ከሕዝብ መጓጓዣ ማዕከሎች ጋር ማገናኘት እና የአውቶቡስ መስመሮች መዘግየቶችን መቀነስ።

**የእግረኛ ደህንነት ($193ሚ ዶላር):-** በእግር የሚሄዱ እና የሚያንከባልሉ ሰዎች ወደፈለጉበት ቦታ በደህና እንዲደርሱ የእግረኛ መንገዶችን፣ መሻገሪያዎችን እና የኩርባ መወጣጫዎችን መገንባት እና መጠገን።

**ምልክቶች እና ስራዎች ($100ሚ ዶላር):-** ለደህንነቱ፣ አስተማማኝ እንቅስቃሴ አሁን ያለውን የትራፊክ ምልክቶችን ማስገባት፣ እንደሠራ ማቆየት እና ማሻሻል፤ የእግረኛ እና የብስክሌት ተደራሽነት ምልክቶችን ማሻሻል; እና በትልልቅ ዝግጅቶች፣ ክስተቶች ወቅት፣ እና ወደ ወደብ ውስጥ እና ወደ ውጭ ለሚደረጉ ጉዞዎች የትራፊክ ስራዎችን መደገፍ።

**የብስክሌት ደህንነት ($133.5ሚ ዶላር):-** የሲያትል የተጠበቀ የብስክሌት መስመር መረብን መዘርጋት፤ ትምህርት ቤቶችን ብስክሌት መንገዶችን፣ መተላለፊያዎችን እና የሰፈር አረንጓዴ መንገዶችን ማገናኘት፤ እና አሁን ያሉትን ነባር የብስክሌት መስመሮችን እንዳሉ መጠበቅ እና ማሻሻል።

**የሰዎች መንገዶች እና የህዝብ ቦታዎች ($66.5ሚ ዶላር):-** ሰዎች ለነሱ ልዩ የሆኑትን እና የነቁ ደማቅ ሰፈሮች እና የንግድ ወረዳዎች ደስ ሊሰኙባቸው እንዲችሉ ከንግድ ወረዳዎች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የህዝብ ቦታዎችን ማስተግበር እና መብራት ማሻሻል።

**የተፈጥሮ አየር ንብረት እና የመቋቋም አቅም ($69ሚ ዶላር):-** የተፈጥሮ አየር ንብረት ለውጥን በቀጥታ መፍታት፣ የአየር ብክለትን በመቀነስ እና ዘላቂነት ያልው የመጓጓዣ አማራጮችን ይበልጥ እንዲገኙ ማድረግ።

**የጭነት እና የእቃዎች እንቅስቃሴ ($45ሚ ዶላር):-** የጭነት መኪናዎች እቃዎችን እንዲያቀርቡ እና አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የጭነት ማሻሻያዎችን ማድረግ።

**መልካም አስተዳደር እና የፍትሃዊ እኩልነት ትግበራ ተነሳሽነት:- ($7.5ሚ ዶላር)** ለሲያትል ግብር ከፋዮች እና ለህዝቡ ተጠያቂነትን እና ግልፅነትን ማስጠበቅ።

# የመጓጓዣ ቀረጥ ፕሮጀክት ምሳሌዎች

የመጓጓዣ ቀረጥ SDOT በመላው ከተማ፣ እንዲሁም እንደተጠገኑ የማቆየት ሥራ፣ የተስፋፋ የገንዘብ ድጋፍ የሚያቀርባቸውን ትልቅ እና ትንሽ ልዩ ፕሮጄክቶችን ያካትታል። በመራጮች ከተፈቀደ፣ የመጓጓዣ ቀረጥ በገንዘብ የሚደግፋቸው አንዳንድ መዋዕለ ንዋይ እነሆ እዚህ።

የአውቶቡስ አስተማማኝነት እና ተደራሽነት ለማሻሻል **160** ፕሮጀክቶች

**350** በቀኝ እና ግራ መንገዶች የተከበቡ የከተማ ሕንጻዎች ወሰኖች አዳዲስ የእግረኛ መንገዶች እና **34,000** የእግረኛ መንገድ ጥገና

የዘመነ የምልክት ጊዜ ቆጣሪ በ **40** ኮሪደሮች እና **10** አዲስ የትራፊክ ምልክቶች ላይ

**15** የተጨናነቀ መንገዶችን እንደገና ቅየሳ እና ንጣፍ ማድረግ

**5** አዲስ የሰፈር አረንጓዴ መንገዶች

የጭነት እንቅስቃሴን ለመደገፍ **32** መዋዕለ ንዋዮች

ወደ እና ከ የሕዝብ መጓጓዣ ማቆሚያዎች የሚያመራ የእግረኛ መብራት

ወደ ሕዝብ ትምህርት ቤቶች በእግር መሄድ፣ ማንከባለል እና ብስክሌት መጋለብ የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ **70** ፕሮጀክቶች

ዛፎችን መትከል እና የተለያዩትን የዛፍ ዝርያዎች ማስፋፋት

ለ**30%** የተጠበቀው የብስክሌት መስመር አውታር የብስክሌት እንቅፋቶች ተሻሽሏል

ለከተማው **134** ድልድዮች ገና ብልሽት ሳይደርስ መከላከያ ጥገና

የህዝብ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሃይል መሙያ መሠረተ ልማት

**12** የደህንነት ኮሪደሮች




**የታቀዱ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን አጠቃላይ ዝርዝር ለማየት፣ የመጓጓዣ ቀረጥ ማጠቃለያውን ከዚህ በታች ባለው ድህረ ገጽ ጣቢያ ይመልከቱ።**

www.seattle.gov/transportation/levy • MoveSeattle@seattle.gov • (206) 319-5893